# ከዙልሂጃ ወር የመጀመሪያዎቹ አስር
# ቀናት ያላቸው ቱሩፋት

የዙል ሂጃ ወር በሂጅሪያ አቆጣጠር 12ኛውና የመጨረሻው ወር ሲሆን ከዚህ ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በኢስላም ትልቅ ቦታ ተሰጥቷቸው እናገኛለን። እነዚህን ቀናት ልዩ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል፡

1) አሏህ የማለባቸው ቀናት መሆናቸው፤ አሏህ በሱረቱል ፈጅር እንዲህ ብሏል፡

قال تعالى [وَٱلۡفَجۡرِ ١ وَلَيَالٍ عَشۡرٖ ٢] الفجر:2&1

ትርጉም ***"በፈጅር እምላለሁ፤ በአስሩ ሌሊቶችም እንዲሁ"*** አል-ፈጅር፥1&2

የቁርአን ተንታኞች አስሩ ሌሊቶች የተፈለጉበት የዙል ሂጃ የመጀመሪያዎቹ አስሮቹ ናቸው ብለዋል። የኢስላም ምሁራን እንዳሉት ደግሞ አሏህ የሚምለው እርሱ ዘንድ ትልቅ ግምት በሚሰጣቸው ነገሮች ነው።

***አስተውሉ፡ አሏህ በቁርአን ላይ በተለያዩ ፍጥረታቱ ሲምል እናስተውላለን፤ እኛ ፍጡራን ግን መማል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የምንምለው በአሏህ እንጅ በፍጡር መማል አንችልም።***

2) እነዚህን ቀናት ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም በዱኒያ ካሉት ቀናት ሁሉ በላጭ እንደሆኑ ስለተናገሩ፤ ተወዳጁ ነቢይ ዐለይሂ ሶላቱ ወሰላም እንዲህ አሉ፡

«**أَفْضَلُ أَيَّامِ الدُّنْيَا أَيَّامُ الْعَشْرِ**»، يَعْنِي: عَشْرَ ذِي الْحَجَّةِ. رَوَاهُ البزارُ في مسندِهِ بإسنادٍ حسنٍ كما قال المنذريُّ في التّرغيبِ

ትርጉም ***"ከዱንያ ቀናት ሁሉ በላጮቹ የዙል ሂጃ የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ናቸው"*** በዛር ዘግበውታል

3) ታላቁ የኢስላም ማእዘን የሆነው ሀጅ የሚከናወነው በነዚህ ቀናት ውስጥ መሆኑ

4) **"የዐረፋን ቀን የጾመ የሁለት አመት ወንጀሉ ይማርለታል"** በማለት ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም የተናገሩለት የዐረፋ ቀን በነዚህ ቀናት ውስጥ መሆኑ

5) እንዲሁም ታላቁ የሙስሊሞች ዒድ የሆነው **ዒድ አል አ**ḍ**ሀ** የሚሆነው ከነዚህ አስር ቀናት ውስጥ ባንዱ መሆኑ እና ሊሎችም ነገሮች እነዚህን ቀናት ልዩ ያደርጋቸዋል።

## በነዚህ ቀናት እኛ ምን
## ማድረግ አለብን

በነዚህ ልዩ ቀናት እኛ ሙስሊሞች ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ መልካም ስራዎችን ማብዛት ይኖርብናል። ተወዳጁ ነቢይ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም በሀዲሳቸው እንዲህ አሉ፡

**"مَا مِنْ أيامٍ أعظمُ عندَ الله ولا أحبُّ إليه العَمَلُ فيهنَّ مِنْ هذه الأيام العَشْرِ فأكثروا فيهنَّ مِنَ التَّهليلِ والتكبيرِ والتَّحمِيد"**.راه الإمامُ أحمدُ

ትርጉም **"እንደነዚህ አስር ቀናት አሏህ ዘንድ የላቁና መልካም ስራዎች የሚወደዱባቸው ቀናት የሉም፤ ላኢላሀ ኢለሏህ፣ አሏሁ አክበር እና አልሀምዱሊላህ ማለትንም አብዙ"** አል ኢማሙ አህመድ ዘግበውታል
አል ሃፊዞ ኢብኑ ሀጀር የተባሉ ታላቅ የኢስላም ምሁር እንዲህ አሉ:

قال ابنُ حجرٍ في فتح الباري: **"وَالَّذِي يَظْهَرُ أَنَّ السَّبَبَ فِي امْتِيَازِ عَشْرِ ذِي الْحِجَّةِ لِمَكَانِ اجْتِمَاعِ أُمَّهَاتِ الْعِبَادَةِ فِيهِ وَهِيَ الصَّلَاةُ وَالصِّيَامُ وَالصَّدَقَةُ وَالْحَجُّ وَلَا يَتَأَتَّى ذَلِكَ فِي غَيْرِهِ"**.

**ትርጉም “የዙል ሂጃ አስር ቀናት የተለዩበት ዋናው ምክኒያት ታላላቅ የሆኑ የዒባዳ አይነቶች ስለተሰባሰቡበት ነው፤ እነዚህም ሶላት፣ጾም፤ ሶደቃና ሀጅ ሲሆኑ ይህ ስብስብ ደግሞ ከነዚህ ቀናት ውጭ በየቱኛውም ጊዜ ሊኖር አይችልም”**

ውድ ወንድሞቸና እህቶቾ በነዚህ ቀናት ልናበዛቸው ከሚገቡ ነገሮች መካከል፡

- ቀዷ ያላወጣናቸው ሶላቶች ካሉ በማውጣት ላይ መትጋት፤
- ግዴታ የሆነብንን እውቀት በመማር ላይ መበርታት፤
- ጾም በመጾም ላይ መጠንከር፤
- ቁርአን በመቅራት ላይ መበርታት፤
- ምላሳችንን በዚክር ማርጠብ፤ በተለይም ላኢላህ ኢለሏህ፣አሏሁ አክበር እና አልሀምዱሊላህ ማለትን ማብዛት፤
- ሶደቃ መስጠትን ማብዛት፤
- ለወላጆች በጎ መዋል፤
- ዝምድና መቀጠል፤
- ያስቀየምነው ሰው ካለ ይቅርታ መጠየቅ እና ሌሎች መልካም ስራዎችንም በመስራት ላይ መበርታት የኖርብናል።

## የሙስሊሞች ዐቂዳ

## በቁርአን

አሏህ እንዲህ አለ

**قل هو الله أحد**

**ይህም ማለት “አሏህ ብቸኛና አጋር የለለው ጌታ ነው፤ የአሏህ እውነታ የፍጡራንን እውነታ አይመስልም፤ የአሏህ ባህሪያትም የፍጡራንን ባህሪያት አይመስሉም፤ የአሏህ ድርጊትም የፍጡራንን ድርጊት አይመስልም።”**

አሏህ እንዲህ አለ

الله الصمد

ይህም ማለት "ሁሉም ፍጡራን ከአሏህ ፈላጊዎች ሲሆኑ እርሱ አሏህ ግን ከፍጡራን ፈጽሞ አይፈልግም። የሰው ልጅን፣ መላኢኮችን፣ አጋንንትንና እንስሣትን የፈጠራቸው አሏህ ስለሆነ ከነርሱ ፈላጊ አይደለም። እንዲሁም የምድር፣ የሰማይ፣ የዐርሽ የኩርሲይና የሌሎች ቦታዎችም ፈጣሪ አሏህ ስለሆነ ከነዚህ ቦታዎች አይፈልግም። አሏህ ቦታዎችን ሳይፈጥር ያለ ቦታ እንደነበረ ሁሉ ለዘላለሙ ያለቦታ የሚኖር ጌታ ነው።"

አሏህ እንዲህ አለ

لم يلد ولم يولد

ይህም ማለት "አባት ለልጁ መሰረት እንደሆነው፤ አሏህ ግን የአንድም ነገር መሰረት ነው አይባልም፤ እንዲሁም ልጅ ያባቱ ቅርንጫፍ እንደሆነው አሏህ የአንድ ነገር ቅርንጫፍ ነው አይባልም። ባጠቃላይ አሏህ አልወለደም፣ አልተወለደም፣ የሚከፋፈል ጌታም አይደለም"

አሏህ እንዲህ አለ

ولم يكن له كفوا أحد

ይህም ማለት "አሏህ አንድም አምሳያ የለውም ማለት ነው። ፊት፣ እጅ፣ እግር፣ ጆሮ፣ ዐይን እና የመሳሰሉት የአካል ክፍሎች የኛ የፍጡራን መገለጫዎች ናቸውና አሏህ በነዚህ የአካል ክፍሎች አይገለጽም። እንዲሁም መቀመጥ፣ መደላደል፣ መውጣት መውረድ የኛ የፍጡራን ባህሪያት ናቸውና አሏህ በነዚህ ባህሪያት አይገለጽም"

አሏህ ቅኑ መንገድ ላይ ጸንተው ከሚሞቱት ያድርገን!!

## አስገራሚ ታሪክ

ከሞንጎላውያን መሪዎች መካከል አንዱ የክርስትና ሀይማኖትን ተቀብሎ ስለነበር የተወሰኑ የእምነቱ መሪዎች በርሱ ዙሪያ ነበሩ። በዚህ ሁኔታ

ላይ እያሉ ከነዚያ የክርስቲያን መሪዎች አንዱ ተወዳጁን ነቢይ ዐለይሂሶላቱ ወሰላም መዝለፍ ጀመረ። እዚያው አካባቢ ለአደን የተዘጋጀ የሆነ ውሻ ታስሮ ነበር። ከዚያ ይህ ሰው ነቢዩን ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም በጣም ሲዛለፍ ይህ ውሻ ዘሎ ተከመረበት። ከዚያም አብረው የነበሩት ሰዎች እንደምንም ብለው ከንክሻው አስለቀቁት። ከዚያም ቦታው ከነበሩት አንዱ ይህ ውሻ የነከሰህ ሙሀመድን ስለዘለፍክ ነው አለው። ይህ ሰው በእብሪት ተወጥሮ አይ ይህ ውሻ የነከሰኝ ወደሱ ሳመለክት ስለነበር ልመታው የፈለግኩት መስሎት ነው እጅ ሙሀመድን ስለዘለፍኩ አይደለም አለና አሁንም ድጋሚ ዘለፋውን ቀጠለበት። ድጋሚ አሁንም ውሻው ዘሎ ተከመረበትና ማንቁርቱን ነቅሎ ሲጥለው ወዲያውኑ ሞተ። ይህን ክስተት ያዩ 40 000 የሚጠጉ ሞንጎላውያን እስልምናን ተቀበሉ አሏሁ አክበር!!